Temari.et

# Amharic, 2015 EC, Grade 8 national exam

Grade 8 · Amharic · 2015 E.C.

**Time allowed:** 120 minutes **Questions:** 56 **Total marks:** 56

Name ____________ Grade ________ ID No. ________ Date ________

**1.** አስቴር ባተሌ በመሆኗ በባልደረቦቿ የተመሰከረላት መምህርት ነች ።በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ የትኛው ነው? (1)

**A.** ታታሪ **B.** አንጋፋ
**C.** ሰነፍ **D.** ጠንካራ

**2.** "አባይ ሲቀና ቤት ያቀና::" በሚለው አነጋገር የተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ፍቺው ምን ሊሆን ይችላል? (1)

**A.** ታታሪ **B.** ልማደኛ
**C.** ጠንካራ **D.** ደካማ

**3.** "ከንጽህና ጉድለት የተነሳ ወባውን በላው::" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ዐውዳዊ ፍቺው ምንድነው? (1)

**A.** አሳዘነው **B.** ገደለው
**C.** ተመገበው **D.** አሳመመው

**4.** "ማኅበረሰባችን በሀገሩ ጉዳይ ሁለንተናዊ ተሳትፎ ማበርከት አለበት::" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ዐውዳዊ ፍቺው ምንድነው? (1)

**A.** ተናጠላዊ **B.** ግላዊ
**C.** ሁሉ-አቀፍ **D.** የወል

**5.** "ሙዚቃ የሰዎችን መንፈስ ያድሳል::" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል በገባበት ዐውድ ተቃራኒ ፍቺው ምንድነው? (1)

**A.** ያረካል **B.** ያስደስታል
**C.** ይረብሻል **D.** ይገነባል

**6.** ዜጎች የተፈጥሮ እና የሰው ሰራሽ መማረኪያዎችን መንከባከብ ይኖርባቸዋል:: በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል በተመሳሳይ ፍቺነት የሚቀርበው የትኛው ነው? (1)

**A.** ሀብቶቻችንን **B.** መስህቦቻችንን
**C.** ቅርሶቻችንን **D.** ጥሪቶቻችንን

**7.** 7. "ይህን ፈተና ለማለፍ ከነበረው ጉጉት የተነሳ ወጥሮ ነው ያጠናው።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺው ምንድን ነው? (1)

**A.** ተግቶ **B.** ደክሞ
**C.** ተዘናግቶ **D.** አከርክሮ

**8.** 8. "እናቱ የሀገርን ደህንነት ለሚጠብቀው ወታደር አገልግል ላከችለት። በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺው ምንድን ነው? (1)

**A.** ብስራት **B.** ደብዳቤ
**C.** መርዶ **D.** ስንቅ

**9.** 9. "መደመም" በሚለው ቃል ከሚከተሉት መካከል ተመሳሳይ ፍቺው ሊሆን የሚችለው የትኛው አማራጭ ነው? (1)

**A.** መደነቅ **B.** መወሸከት
**C.** መልፋት **D.** መድገም

**10.** 10. "ቃላት በተለያዩ ዐውድ ሲገኙ የተለያዩ ፍቺ ሊሰጡ ይችላሉ።" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺው -------ነው። (1)

**A.** አገባብ **B.** አቅጣጫ
**C.** ዘውግ **D.** ስፍራ

**11.** 11. ከጎንደር ወደ ባህርዳር የሚወስደው ------- በመፈራረሱ እየተጠገነ ነው፡፡ (1)

**A.** ትምህርት ቤት
**B.** ፍርድ ቤት
**C.** አውራ-ጎዳና
**D.** ቤተ- መጻሕፍት

**12.** 12. የሀገራችን --------- እድገት በዜጎቻችን ኑሮ ላይ ለውጥ ማምጣት አለበት፡፡ ከቀረቡት አማራጮች መካከል በባዶ ቦታው መግባት ያለበት የቱ ነው? (1)

**A.** ብልጽግናዊ
**B.** አገልግሎታዊ
**C.** መንፈሳዊ
**D.** ምጣኔ-ሀብታዊ

**13.** *ብልሃት፤ ወደፊት በገጸባሕርያት ገጠመኝ ውስጥ ሊከሰቱ የታሰቡትን ቁልፍ ክስተቶች (እንደ ትንቢት ብጤ ነው ነገሩ) ለማመልከትም ያግዛል፤ያለፈውን ገጠመኞቻቸውንና ፍላጎታቸውን በመነሻነት ተጠቅሞ የሚቀርብ ነው፡፡ ይህ በኢዲፐስ ውስጥ በጉልህ ይታያል፡፡ ወደ መገባደጃው አካባቢ፤የዋናው ገጸባሕርይ (የኢዲፐስ) ድቀት ከምን ሊመነጭ እንደቻለ የሚነገረው፤ከልጅነት ጀምሮ የነበረውን የሕይወት ገጠመኝና ያም እንዲይቀሰቀፍ ለዚህ ሁሉ ጣጣ እንዳይበቃው በመተረክ ነው፡፡ የመጋረጃ ጀርባ ክንዋኔዎች ዝግም በተውኔት ትረካ አቀራረብ ውስጥ እንደ ብልሃት ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በጸጋዬ ገብረ መድኅን የክርም ሰው ውስጥ፤ሞገሴ ሚስቱ በግርድና ተቀጥራ ከምትሠራበት (በኋላም ሚስት "ከሆነችበት") ቤት ሄዶ፤የተመለከተው ጉድ የቀረበው በሞገሴ ትረካ ነው፡፡ አንዳንድም፤ በመደረክ ላይ ሲከወኑ የሚያስቸግሩ (ለምሳሌ በጥንታዊ ትራጄዲ የኖረ ሰቀቀን የሚፈጥሩ እንደ ግድያ፤ታንቆ መሞት፤በጥይት መመታት፤ወዘተ፤የመሳሰሉ) ድርጊቶች ከመጋረጃው ጀርባ እንደተከናወኑ ሆነው ውጤታቸው ብቻ በመደረክ ላይ ይዘገባል፤በገጸባሕርያቱ አንደበት፡፡ ይህ እንግዲህ በተውኔት ጥበብ እንደ የትረካ ብልሃት መሆኑ ነው፡፡ (የሻው ተሰማ፡፡ 2013፡፡ ስነ-ተውኔት ግለ መማሪያ፡፡ ገጽ 40-42)* (1)

14. በምንባቡ መሰረት ተውኔት ከሌሎች የኪነጥበብ ዘውጎች የሚለየው በምንድነው?

**A.** ታሪኩን በሚያቀርቡበት ጥበብ
**B.** በታሪክ አወቃቀሩ
**C.** በግልጽነቱና በቀጥተኝነቱ
**D.** በመድረክ ተመድረኮ በመቅረቡ

**14.** *ብልሃት፤ ወደፊት በገጸባሕርያት ገጠመኝ ውስጥ ሊከሰቱ የታሰቡትን ቁልፍ ክስተቶች (እንደ ትንቢት ብጤ ነው ነገሩ) ለማመልከትም ያግዛል፤ያለፈውን ገጠመኞቻቸውንና ፍላጎታቸውን በመነሻነት ተጠቅሞ የሚቀርብ ነው፡፡ ይህ በኢዲፐስ ውስጥ በጉልህ ይታያል፡፡ ወደ መገባደጃው አካባቢ፤የዋናው ገጸባሕርይ (የኢዲፐስ) ድቀት ከምን ሊመነጭ እንደቻለ የሚነገረው፤ከልጅነት ጀምሮ የነበረውን የሕይወት ገጠመኝና ያም እንዲይቀሰቀፍ ለዚህ ሁሉ ጣጣ እንዳይበቃው በመተረክ ነው፡፡ የመጋረጃ ጀርባ ክንዋኔዎች ዝግም በተውኔት ትረካ አቀራረብ ውስጥ እንደ ብልሃት ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በጸጋዬ ገብረ መድኅን የክርም ሰው ውስጥ፤ሞገሴ ሚስቱ በግርድና ተቀጥራ ከምትሠራበት (በኋላም ሚስት "ከሆነችበት") ቤት ሄዶ፤የተመለከተው ጉድ የቀረበው በሞገሴ ትረካ ነው፡፡ አንዳንድም፤ በመደረክ ላይ ሲከወኑ የሚያስቸግሩ (ለምሳሌ በጥንታዊ ትራጄዲ የኖረ ሰቀቀን የሚፈጥሩ እንደ ግድያ፤ታንቆ መሞት፤በጥይት መመታት፤ወዘተ፤የመሳሰሉ) ድርጊቶች ከመጋረጃው ጀርባ እንደተከናወኑ ሆነው ውጤታቸው ብቻ በመደረክ ላይ ይዘገባል፤በገጸባሕርያቱ አንደበት፡፡ ይህ እንግዲህ በተውኔት ጥበብ እንደ የትረካ ብልሃት መሆኑ ነው፡፡ (የሻው ተሰማ፡፡ 2013፡፡ ስነ-ተውኔት ግለ መማሪያ፡፡ ገጽ 40-42)* (1)

15. በምንባቡ መሰረት ስለ ተውኔት ስህተት የሆነው አገላለጽ የትኛ ነው?

**A.** በትወና ጥበብ በተደራሲና በታሪኩ መካከል ጣልቃ ገብቶ የሚያወጋ ሦስተኛ ወገን ያስፈልጋል፡፡
**B.** በተውኔት ሁነቶችን ለተደራሲ የማቅረብ ሂደት ልዩልዩ መልኮች ይኖራቸዋል፡፡
**C.** በተውኔት ሁነቶችንና ድርጊቶችን አሁን ሲከወኑ ማሳየት ነው፡፡
**D.** በተውኔት የትረካ ሂደቱ ለተደራሲው የሚቀርበው በውጫዊ ሕዋሳቱ እገዛ ነው፡፡

**15.** በምንባቡ መሰረት ስህተት የሆነው የትኛው ነው? (1)

**A.** ሮዶሪጎ ኢያጎን ካመናጨቀው በኋላ፣ በቀጥታ የቅሬታውን መንስኤ በመናገሩ ነው፡፡
**B.** የሮዶሪጎ ሁኔታ ከዋናው የተውኔት አካል በፊት ምን እንደተፈጠረ ይጠቁማል፡፡
**C.** ስለተውኔቱ ዓለም አጠቃላይ መረጃ የሚሰጠው የተውቂያ ደረጃ አለ፡፡
**D.** ተውኔትን ትረካ የሚያደርገው የተውኔቱን መንፈስ መሰረት አለማድረጉ ነው፡፡

**16.** በቀረበው ምንባብ መሰረት ያለፈውን ገጠመኞቻቸውንና ፍላጎታቸውን በመነሻነት ተጠቅሞ በጉልህ የሚታየው በ ----------------አማካኝነት ነው፡፡ (1)

**A.** ኢዲፐስ
**B.** ሮዶሪጎ
**C.** ጸጋዬ
**D.** ኢያጎ

**17.** በምንባቡ መሰረት የቀረቡት የትረካ ስልቶች ስንት ናቸው? (1)

A. ሁለት
B. ሶስት
C. አራት
D. አምስት

**18.** በቀረበው ምንባብ መሰረት ከመጋረጃው ጀርባ እንደተከናወኑ ሆነው ውጤታቸው ብቻ በመድረክ ላይ በገጸ-ባህርያቱ አንደበት የማይዘገበው የትኛው ነው? (1)

A. በጥይት መመታት
B. ታንቆ መሞት
C. ግድያ
D. ፈንጠዝያ

**19.** በምንባቡ መሰረት የመጋረጃ ጀርባ ክዋኔዎች ዘገባም በተውኔት ትረካ አቀራረብ ውስጥ እንደ ----------- ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል፡፡ (1)

A. ብልሃት
B. ጥበብ
C. ሒስ
D. ግጭት

**20.** በምንባቡ መሰረት "...የዋናው ገጸ-ባህርይ ድቀት ከምን ሊመነጭ እንደቻለ የሚነገረው፤ከልጅነት ጀምሮ የነበረውን የሕይወት ገጠመኝና ደም አነሳሱ ለዚህ ሁሉ ጣጣ እንዳበቃው በመተረክ ነው::" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ምንድነው? (1)

A. ብልሽት
B. ውድቀት
C. ክስረት
D. አብረት

**21.** ቀጥለው ከቀረቡት አማራጮች መካከል ለዚህ አጭር ምንባብ የተሻለ ርዕስ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?? (1)

A. መሰረታዊ የተውኔት መዋቅር
B. የተውኔት ግልጽነትና ቀጥተኛነት
C. የተውኔት የአተራረክ ብልሃት
D. የተውኔት ተመድራኪነት

**22.** «ፈታ» የሚለው ቃል «ትዳሩ ተበተነ» የሚል ትርጉም የሚኖረው በየትኛው አረፍተ ነገር ውስጥ ሲገባ ነው? (1)

A. በግ የታሰረበትን ገመድ ፈታ::
B. ከብህትውና በኋላ ሚስቱን ፈታ::
C. በአባቱ ሃብት ፈታ ብሎ ይኖራል::
D. በዓሉን አስመልክቶ መንግስት እስረኞችን ፈታ

**23.** ከሚከተሉት መካከል «ዓይነ-ልብ» ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ተመሳሳይ ፍቺ--------- ነው:: (1)

A. ተንኮለኛ
B. ቆንጆ
C. ነገረኛ
D. ምቀኛ

**24.** ከሚከተሉት መካከል ቃለ መጠይቅ በሚደረግበት ወቅት መከናወን ያለበት የትኛው ተግባር ነው? (1)

A. ለቃለ መጠይቁ የሚሆኑ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት
B. የቃለ መጠይቁን ሂደት በድምጽና በምስል መቅረጫ መቅረጽ
C. ለቃለ መጠይቁ ተሳታፊ የሆኑ አካላትን ማመስገን
D. ቃለ መጠይቅ የሚያደርገው አካል ከቃለ መጠይቁ በፊት በቂ ዝግጅት ማድረግ

**25.** ከቀረቡት አማራጮች መካከል ስለክርክር ትክክል የሆነው የትኛው ነው? (1)

A. ተከራካሪው ለሚያነሳው ሀሳብ እውነተኛ መረጃ ማቅረብ
B. ክርክሩ በምክንያታዊነት ተደግፎ አለመቅረቡ
C. ተከራካሪው ከእሱ በተቃራኒ ለቆመው ወገን ማስረጃ በማቅረብ መደገፍ
D. ክርክር የሚያደርገው አካል ያለ በቂ ዝግጅት መቅረብ

**26.** ...«ሴቶችም በዘመናዊ ሥልጣኔ እየገፉ ሄደው ለተማሩ ባሎቻቸው ድጋፍ፣ ለአገራቸው ልማት፣ ለመንግስታቸው ኩራትና ትምክህት እንዲበቁ ይጥሩ ነበር :: ግርማዊት እቴጌ መነን በ1954 ዓ.ም የካቲት 8 ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ::» ይህ አንቀጽ በምን ስልት የቀረበ ነው? (1)

A. ገላጭ
B. አመዛዛኝ
C. ተራኪ
D. ስዕላዊ

**27.** ከሚከተሉት መካከል ስዕላዊ አንቀጽ ለመጻፍ እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል የሚችለው ሃሳብ የትኛው ነው? (1)

**A.** የኑሮ ውድነትን ሁሉም ሰው ሊከላከልው የሚገባው ነው::
**B.** የሃገር ሰላም ከሁሉም ነገር በላይ ይቀድማል::
**C.** የኮቪድ-19 ስርጭት አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል::
**D.** አይኖቿን አፍጥጣ ቀጥታ ወደ እኔ መጣች ::

**28.** “ሜላት የደስደስ ያላት መልካም ልጅ ነች::” በሚል ዐረፍተ ነገር የተጀመረ አንቀጽ ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የቱን ሃሳብ በዝርዝሩ ውስጥ ሊያካትት አይችልም:: (1)

**A.** ዓይነ መልካም ልጅ ነች::
**B.** በጠባይዋ ጨዋ ልጅ ነች::
**C.** ፕሮሴንቴጅት ልጅ ነች::
**D.** ተረክዘህ ለሚ ልጅ ነች::

**29.** ከተዘረዘሩት ዐረፍተ ነገሮች መካከል ውስብስብ የሆነው የትኛው ነው? (1)

**A.** ያ ጎበዝ የዘነበ ልጅ ነጋዴ ነው::
**B.** አለማዘዝ ምስጉን መምህርት ነች::
**C.** አለሚቱ በማጥናቷ ውጤት አመጣች::
**D.** እነዚህ የሳቴ ልጆች በጣም ጎበዞች ናቸው::

**30.** 32. ከሚከተሉት ውስጥ በስርዓተ ነጥብ አጠቃቀሙ ትክክል የሆነው የትኛው አማራጭ ነው? (1)

**A.** ገበሬው የቅባት እህሎችን ኑግ፤ ተልባ፤ ሱፍ እና ሰሊጥ ወደ ገበያወስዶ አቀና።
**B.** ገበሬው የቅባት እህሎችን ኑግ፤ ተልባ፤ ሱፍናሰሊጥ ወደ ገበያወስዶ አቀና።
**C.** ገበሬው የቅባት እህሎችን ኑግ፤ ተልባ፤ ሱፍ፤ እና ሰሊጥ ወደ ገበያ ወስዶ አቀና።
**D.** ገበሬው የቅባት እህሎችን ኑግ፤ ተልባ፤ ሱፍና ሰሊጥ ወደ ገበያ ወስዶ አቀና።

**31.** 33. የምክንያትና የውጤት ግንኙነቱ ያልተጣጣመው ከሚከተሉት መካከል በየትኛው አማራጭ ነው? (1)

**A.** ሰላም ቆንጆ ልጅ ናት፤ ስለዚህ ጎበዝ ኳስ ተጫዋች ትሆናለች።
**B.** ማርታ የኳስ ልምምድ ታደርጋለች፤ ስለዚህ ውጪ ሀገር ትሄዳለች።
**C.** አልማዝ ጉንፋን ይዟታል፤ ስለዚህ ታምማለች።
**D.** አየለ ተኝቶ ያጠናል፤ ስለዚህ ወደ መዝናኛ ሥራ ይሄዳል።

**32.** 34. ቀይማ ቀይ ነህ የበርበሬ ፍሬ፤ ኮከብንስ እንጂ እንደ አባ ጨሬ። በሚል የቀረበው የቃል ግጥም ከሚከተሉት መካከል የትኛውን ሃሳብ መሰረት አድርጎ የተነገረ ነው? (1)

**A.** ፍቅርን
**B.** ብቀላን
**C.** ጥላቻን
**D.** ሃዘንታን

**33.** 35. ከቀረቡት አረፍተ ነገሮች መካከል ተገብሮ የሆነው የትኛው ነው? (1)

**A.** አስቴር ዛሬ ሀብል ሸመተች።
**B.** አየለ ዛሬ በግ ገዛ።
**C.** ዓለሙ ዛሬ እህል ሸመተ ።
**D.** አልማዝ ዛሬ ብር ተሰረቀች

**34.** 36. ዓላማ ያለው ጊዜና ቦታ የተወሰነለት አንድና ከአንድ በላይ በሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ ሰዎች ሀሳባቸውን የሚለዋወጡበት እና ወደ ጋራ መግባባት ላይ የሚደርሱበት------------------ ነው። (1)

**A.** ውይይት
**B.** ክርክር
**C.** ቃለ መጠይቅ
**D.** ንግግር

**35.** 37 "ቆቅ" የሚለውን ቃል አማራጭያዊ እና ፍንጭአዊ ፍቺን በሚመለከት ትክክል የሆነው የትኛው አማራጭ ነው? (1)

**A.** ቆቅ የሚለው ቃል አማራጭያዊ ፍቺ ንቁ የሚል ነው።
**B.** ቆቅ የሚለው ቃል ፍንጭአዊ ፍቺ ከወፍ ዘሮች አንዱ ነው የሚል ነው።
**C.** ቆቅ የሚለው ቃል አማራጭያዊ ፍቺ ጎበዝ የሚል ነው። ::
**D.** ቆቅ የሚለው ቃል ፍንጭአዊ ፍቺ ንቁ የሚል ነው።

**36.** 38. "የቆጡን አውርድ ብላ የብብቷን ጣለች፤" ከሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ጋር በፍቺ ተመሳሳይ የሆነው የትኛው ነው? (1)

**A.** የባግዳድን ልጅ ውሀ መጣው::
**B.** የላምን ልጅ ቅማል በላው::
**C.** ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም::
**D.** አትርፍ ባይ አጉዳይ ::

**37.** 39. "እሩቅ" የሚለው የሥርዓተ-ነጥብ ከቀረቡት አማራጮች መካከል የትኛውን ይወክላል? (1)

**A.** ትዕምርተ-ስላት

**B.** እኩል ይሆናል

**C.** ቃል አጋኖ

**D.** ንዑስ ሰረዝ

**38.** 40. "እናቴ የሰማይ ስባሪ የሚያህል ዳቦ ሰጠችኝ::" በሚለው ዓረፍተ ነገር የተገለጠው የዘይቤ ዓይነት ከቀረቡት አማራጮች መካከል በየትኛው ነው? (1)

**A.** ሰውኛ ዘይቤ

**B.** ተለዋጭ ዘይቤ

**C.** ተነጻጻሪ ዘይቤ

**D.** ግነት ዘይቤ

**39.** 41 አስቴር ጎበዝ ተማሪ ነች፤ ------- በፈተናው ከፍተኛ ውጤት አላመጣችም። በባዶ ቦታው መግባት ያለበት አያያዥ የቱ ነው? (1)

**A.** ስለዚህ

**B.** ካልሆነ ግን

**C.** ነገር ግን

**D.** እስከዚያ

**40.** 42. ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው? (1)

**A.** ለምን ትምህርታችሁን አታጠኑም?

**B.** ትምህርታችሁን ተግታችሁ አጥኑ!

**C.** ትምህርታችሁን ብታጠኑ መልካም ነው።::

**D.** ትምህርታችሁን እንዴት ነው የምታጠኑት?

**41.** 44. "ዓለሙ <u>እኩይ</u> ባህሪ ስላለው በጓደኞቹ ዘንድ ተቀባይነቱ አጠራጣሪ ነው።" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ፍቺ-----------ነው። (1)

**A.** መጥፎ፤

**B.** ተንኮለኛ፤

**C.** ጥሩ፤

**D.** ሰናይ፤

**42.** *መመሪያ አምስት፡- ከተራቁጥር 45 እና 46 ቀጥሎ በቀረበው ምልልስ መሰረት መልስ/ሺ። ዘሩ፡-ከጽዳት ጋር ለሚፈጠረው ችግር ሁሉ ተጠያቂው እጅ ነው። ምክንያቱም እጅ የተለያዩ ነገሮችን በመንካት ራሱን ያቆሽሻል። አፍንጫንም፣ ጆሮንም፣ ዓይንንም፣ አፍንም፣ ገላንም፣ ጸጉርንም... የመንካት ችግር አለበት። በመሆኑም ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እጅ ከሰዎች የአካል ክፍሎች መገንጠል አለበት በማለት በዛሬው ዕለት ሰልፍ እንደሚወጡ ታውቋል። እኔም የሰልፉን ተገቢነት አምንበታለሁ። አንቺስ? ገሊላ፡- ለሚፈጠረው ችግር ሁሉ ተጠያቂዎቹ ሰልፈኞቹ ራሳቸው ናቸው። እጅ የሚቆሽሸው ሥራ ሲሰራ ነው። ያርሳል፣ ያርማል፣ ያጭዳል፣ ቤት ያጸዳል...። እነዚህ ሥራዎች ደግሞ በባህሪያቸው የሚያቆሽሹ ናቸው። እጅ ዓይንን፣ አፍንጫን፣ ጆሮን፣ አፍን፣ ጸጉርን .... የሚነካው ሊያጸዳቸው ፈልጎ ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ስለሚከክን ስለሚቆረጥ ነው። ስለዚህ ጥፋተኛው እጅ ሳይሆን ጥፋተኞቹ ራሳቸው ሰልፈኞቹ እና አንተ ናችሁ። እኔ ግን ፈጽሞ በሰልፉ አላምንበትም። አንተም ከራስህ ጋር ብትማከር መልካም ነው። ደግመህ አስብበት።*
45. በዚህ ምልልስ መሰረት ዘሩ ምን የሚል አቋም ያለው ይመስላል? (1)

**A.** ሊካሄድ የታሰበው ሰልፍ አግባብነት የለውም የሚል ነው።

**B.** ለሚፈጠረው ቀውስ ሁሉ እጅን ተጠያቂ ያደርጋል።

**C.** ለሚከናወኑት ስራዎች ሁሉ የእጅን አስፈላጊነት በጽኑ ያምናል።

**D.** ሰልፈኞቹን በጽኑ ይኮንናል።

**43.** *መመሪያ አምስት፡- ከተራቁጥር 45 እና 46 ቀጥሎ በቀረበው ምልልስ መሰረት መልስ/ሺ። ዘሩ፡-ከጽዳት ጋር ለሚፈጠረው ችግር ሁሉ ተጠያቂው እጅ ነው። ምክንያቱም እጅ የተለያዩ ነገሮችን በመንካት ራሱን ያቆሽሻል። አፍንጫንም፣ ጆሮንም፣ ዓይንንም፣ አፍንም፣ ገላንም፣ ጸጉርንም... የመንካት ችግር አለበት። በመሆኑም ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እጅ ከሰዎች የአካል ክፍሎች መገንጠል አለበት በማለት በዛሬው ዕለት ሰልፍ እንደሚወጡ ታውቋል። እኔም የሰልፉን ተገቢነት አምንበታለሁ። አንቺስ? ገሊላ፡- ለሚፈጠረው ችግር ሁሉ ተጠያቂዎቹ ሰልፈኞቹ ራሳቸው ናቸው። እጅ የሚቆሽሸው ሥራ ሲሰራ ነው። ያርሳል፣ ያርማል፣ ያጭዳል፣ ቤት ያጸዳል...። እነዚህ ሥራዎች ደግሞ በባህሪያቸው የሚያቆሽሹ ናቸው። እጅ ዓይንን፣ አፍንጫን፣ ጆሮን፣ አፍን፣ ጸጉርን .... የሚነካው ሊያጸዳቸው ፈልጎ ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ስለሚከክን ስለሚቆረጥ ነው። ስለዚህ ጥፋተኛው እጅ ሳይሆን ጥፋተኞቹ ራሳቸው ሰልፈኞቹ እና አንተ ናችሁ። እኔ ግን ፈጽሞ በሰልፉ አላምንበትም። አንተም ከራስህ ጋር ብትማከር መልካም ነው። ደግመህ አስብበት።*
46. በዚህ ምልልስ መሰረት ገሊላ ምን ዓይነት ባህሪ እንዳላት መገመት ይቻላል? (1)

**A.** በተጠያቂነትና በምክንያታዊነት የምታምን ሴት ነች።

**B.** የምታቀርባቸው ሀሳቦች የሚያሳምኑ አይደሉም።

**C.** ከዘሩ ይልቅ ገሊላ የምታቀርበው ሀሳብ አያሳምንም።

**D.** ሰልፈኞቹ ሊያካሂዱት ያሰቡትን ሰልፍ የምትደግፍ ነች።

**44.** *ተራቁተሽ ታርዘሽ፤ ባይሽ ከሰው ተራ የምትቀምሽው የለሽ፤ የተገፋ እንጀራ፤ ምዕዋት የተረፈ ሲሳይ የጎደፈ ከሰዉ እጅ ያለፈ፤ ትጠጪው ምን የለሽ፤ ትታጠቢው ውኃ ሆነሽ ያባይ እናት፤ ሆነሽ የሰው ድኻ፤ ባየ ይማም (2013)፤ ትዝብትና ተስፋ ትዝብት፤ ገጽ 128*
የግጥሙ ስሜት ምን ሊሆን ይችላል (1)

**A.** ንዴት

**B.** ስጋት

**C.** ጸጸት

**D.** ጀግንነት

**45.** *ተራቁተሽ ታርዘሽ፤ ባይሽ ከሰው ተራ የምትቀምሽው የለሽ፤ የተገፋ እንጀራ፤ ምዕዋት የተረፈ ሲሳይ የጎደፈ ከሰዉ እጅ ያለፈ፤ ትጠጪው ምን የለሽ፤ ትታጠቢው ውኃ ሆነሽ ያባይ እናት፤ ሆነሽ የሰው ድኻ፤ ባየ ይማም (2013)፤ ትዝብትና ተስፋ ትዝብት፤ ገጽ 128* (1)

ግጥሙ የሚያወራው ማንን ነው?

**A.** ወላጅ እናትን

**B.** ድሃ ሴትን

**C.** ኢትዮጵያን

**D.** አፍሪካን

---

**46.** *ተራቁተሽ ታርዘሽ፤ ባይሽ ከሰው ተራ የምትቀምሽው የለሽ፤ የተገፋ እንጀራ፤ ምዕዋት የተረፈ ሲሳይ የጎደፈ ከሰዉ እጅ ያለፈ፤ ትጠጪው ምን የለሽ፤ ትታጠቢው ውኃ ሆነሽ ያባይ እናት፤ ሆነሽ የሰው ድኻ፤ ባየ ይማም (2013)፤ ትዝብትና ተስፋ ትዝብት፤ ገጽ 128* (1)

በግጥሙ መሰረት «ታርዘሽ» የሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺው ምንድን ነው?

**A.** ለብሰሽ

**B.** ጠግበሽ

**C.** ወፍረሽ

**D.** ተራቁተሽ

---

**47.** *ተራቁተሽ ታርዘሽ፤ ባይሽ ከሰው ተራ የምትቀምሽው የለሽ፤ የተገፋ እንጀራ፤ ምዕዋት የተረፈ ሲሳይ የጎደፈ ከሰዉ እጅ ያለፈ፤ ትጠጪው ምን የለሽ፤ ትታጠቢው ውኃ ሆነሽ ያባይ እናት፤ ሆነሽ የሰው ድኻ፤ ባየ ይማም (2013)፤ ትዝብትና ተስፋ ትዝብት፤ ገጽ 128* (1)

የግጥሙ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

**A.** እናትና ሃገር ሁልጊዜም ቢሆን ለችግር የተጋለጡ ናቸው፡፡

**B.** ሃገራችን የተትረፈረፈ ሃብት ቢኖራትም ደሆች ግን ተርበዋል፡፡

**C.** ሃገራችን በአባይ ወንዝ ምክንያት ለችግር እየተጋለጠች ነው፡፡

**D.** ሃገራችን የውሃና የሰው ሃብት ቢኖራትም ከችግር አልተላቀቀችም፡፡

---

**48.** *በአንድ ሰፊ አገር አንድ ሀብታም በአህያ፤ በላም፤ በበሬ፤ በግመል፤ በፍየል፤ በበግ፤ በከብቱ በማናቸውም ሁሉ የደሰ ደስ ያለው ከበርቴ ነበር ይባላል:: ሌቦች ስንኳንስ ከሀብታም ከድሃም ቢሆን ሌባ መስረቅ ልማዱ ነውና ሌቦች ባንድነት ተማክረው ሌት ከቤት ገብተው ከብቶቹን ከገንዘቡ ሰርቀው ይዘው ወደ በረሃ ገቡ:: ከበረሃም ሆነው ሁለቱ ሌቦች ሶስተኛውን ወደ ከተማ በሰውር ምግብ ገዝቶ እንዲያመጣላቸው ላኩት:: ከሄደም በኋላ እነዚህ ከበረሃ የቀሩት እንዲህ ብለው እርስ በእርሳቸው ተማከሩ:: ሶስተኛውን ጓደኛችንን ሳንጨምር ይህን ሁሉ ገንዘብ ብንካፈለው ብዙ ይጠቅመናል:: ይኸውም ባልንጀራን ሲመጣ ተደብቀን እንግደለው ብለው ሐሳባቸውን ጨረሱ:: ያኛውም ወደ ላኩት ሥፍራ ሲሄድ ለራሱ እንዲህ ያስብ ነበር መቼም ፋንታዬን ባልጄ ነውና የምመለስ እነሱን በዚህ በምወስድላቸው ምግብ ላይ መርዝ ገዝቼና ነስንሼ ፈጅቼአቸው ገንዘቡን ሁሉ ለብቻዬ እወስዳለሁ ብሎ እንዳሰበው አድርጎ ሲመለስ ከእነሱ ዘንድ ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው ገደሉትና በልተውት በአንድ ሰዓት ከሄዱ በኋላ እየተንጨጨፉ ሞቱ:: እነዚያም ለሁለት እሱም ለራሱ ሲያስብ ምንም ሳያገኙ ጠፍተው የሁሉም ሌቦች ሬሳ ከዚያው ተገኘ:: የተሰረቀውም ገንዘብ ሳንቲም እንኳ ሳይጐድል አብረዋቸው ባንድነት ተገኝቶ ለዋና ባለቤቱ ነጻ ገንዘቡ ተመለሰለት ይባላል:: የሌባ ትርፍ ጥፋቱ ነው:: የሰው ገንዘብ በከንቱ ቢሄድ አለመጠቀሙን እኒህ ምሳሌዎች ያስረዳሉ::* (1)

በምንባቡ መሰረት ከበርቴው ከነበሩት የእንስሳት ሀብቶች መካከል ያልተጠቀሰው የትኛው ነው?

**A.** ግመል

**B.** ፍየል

**C.** በቅሎ

**D.** በሬ

---

**49.** *በአንድ ሰፊ አገር አንድ ሀብታም በአህያ፤ በላም፤ በበሬ፤ በግመል፤ በፍየል፤ በበግ፤ በከብቱ በማናቸውም ሁሉ የደሰ ደስ ያለው ከበርቴ ነበር ይባላል:: ሌቦች ስንኳንስ ከሀብታም ከድሃም ቢሆን ሌባ መስረቅ ልማዱ ነውና ሌቦች ባንድነት ተማክረው ሌት ከቤት ገብተው ከብቶቹን ከገንዘቡ ሰርቀው ይዘው ወደ በረሃ ገቡ:: ከበረሃም ሆነው ሁለቱ ሌቦች ሶስተኛውን ወደ ከተማ በሰውር ምግብ ገዝቶ እንዲያመጣላቸው ላኩት:: ከሄደም በኋላ እነዚህ ከበረሃ የቀሩት እንዲህ ብለው እርስ በእርሳቸው ተማከሩ:: ሶስተኛውን ጓደኛችንን ሳንጨምር ይህን ሁሉ ገንዘብ ብንካፈለው ብዙ ይጠቅመናል:: ይኸውም ባልንጀራን ሲመጣ ተደብቀን እንግደለው ብለው ሐሳባቸውን ጨረሱ:: ያኛውም ወደ ላኩት ሥፍራ ሲሄድ ለራሱ እንዲህ ያስብ ነበር መቼም ፋንታዬን ባልጄ ነውና የምመለስ እነሱን በዚህ በምወስድላቸው ምግብ ላይ መርዝ ገዝቼና ነስንሼ ፈጅቼአቸው ገንዘቡን ሁሉ ለብቻዬ እወስዳለሁ ብሎ እንዳሰበው አድርጎ ሲመለስ ከእነሱ ዘንድ ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው ገደሉትና በልተውት በአንድ ሰዓት ከሄዱ በኋላ እየተንጨጨፉ ሞቱ:: እነዚያም ለሁለት እሱም ለራሱ ሲያስብ ምንም ሳያገኙ ጠፍተው የሁሉም ሌቦች ሬሳ ከዚያው ተገኘ:: የተሰረቀውም ገንዘብ ሳንቲም እንኳ ሳይጐድል አብረዋቸው ባንድነት ተገኝቶ ለዋና ባለቤቱ ነጻ ገንዘቡ ተመለሰለት ይባላል:: የሌባ ትርፍ ጥፋቱ ነው:: የሰው ገንዘብ በከንቱ ቢሄድ አለመጠቀሙን እኒህ ምሳሌዎች ያስረዳሉ::* (1)

በምንባቡ መሰረት ሌቦች የሰረቁትን ከብትና ገንዘብ ወደየት ነው የወሰዱት?

**A.** ጫካ

**B.** በረሃ

**C.** ገበያ

**D.** ወንዝ

**50.** *በአንድ ሰፊ አገር አንድ ሀብታም በአህያ፤ በላም፤ በበሬ፤ በግመል፤ በፍየል፤ በበግ፤ በከብቱ በማናቸውም ሁሉ የደሰ ደስ ያለው ከበርቴ ነበር ይባላል:: ሌቦች ስንኳንስ ከሀብታም ከድሃም ቢሆን ሌባ መስረቅ ልማዱ ነውና ሌቦች ባንድነት ተማክረው ሌት ከቤት ገብተው ከብቶቹን ከገንዘቡ ሰርቀው ይዘው ወደ በረሃ ገቡ:: ከበረሃም ሆነው ሁለቱ ሌቦች ሶስተኛውን ወደ ከተማ በሰውር ምግብ ገዝቶ እንዲያመጣላቸው ላኩት:: ከሄደም በኋላ እነዚህ ከበረሃ የቀሩት እንዲህ ብለው እርስ በእርሳቸው ተማከሩ:: ሶስተኛውን ጓደኛችንን ሳንጨምር ይህን ሁሉ ገንዘብ ብንካፈለው ብዙ ይጠቅመናል:: ይኸውም ባልንጀራን ሲመጣ ተደብቀን እንግደለው ብለው ሐሳባቸውን ጨረሱ:: ያኛውም ወደ ላኩት ሥፍራ ሲሄድ ለራሱ እንዲህ ያስብ ነበር መቼም ፋንታዬን ባልጄ ነውና የምመለስ እነሱን በዚህ በምወስድላቸው ምግብ ላይ መርዝ ገዝቼና ነስንሼ ፈጅቼአቸው ገንዘቡን ሁሉ ለብቻዬ እወስዳለሁ ብሎ እንዳሰበው አድርጎ ሲመለስ ከእነሱ ዘንድ ሊደርስ ጥቂት ሲቀረው ገደሉትና በልተውት በአንድ ሰዓት ከሄዱ በኋላ እየተንጨጨፉ ሞቱ:: እነዚያም ለሁለት እሱም ለራሱ ሲያስብ ምንም ሳያገኙ ጠፍተው የሁሉም ሌቦች ሬሳ ከዚያው ተገኘ:: የተሰረቀውም ገንዘብ ሳንቲም እንኳ ሳይጐድል አብረዋቸው ባንድነት ተገኝቶ ለዋና ባለቤቱ ነጻ ገንዘቡ ተመለሰለት ይባላል:: የሌባ ትርፍ ጥፋቱ ነው:: የሰው ገንዘብ በከንቱ ቢሄድ አለመጠቀሙን እኒህ ምሳሌዎች ያስረዳሉ::* (1)

በምንባቡ መሰረት የቀሩት ሌቦች እርስ በእርሳቸው ምን ብለው ተማከሩ?

**A.** ጓደኛችንን ሳንጨምር ገንዘቡን መካፈል የለብንም::
**B.** ጓደኛችንን ሳንካትት ገንዘቡን እንካፈል::
**C.** ያለ ጓደኛችን ገንዘቡን መካፈል የለብንም::
**D.** ያለ ጓደኛችን ገንዘቡን መካፈል ይጠቅመናል::

**51.** 54. በምንባቡ መሰረት ወደ ከተማ የተላከው ሌባ ምን ብሎ ነው ያሰበው? (1)

**A.** በምወስድላቸው ምግብ ጓደኞቼን እጠግባቸዋለሁ።
**B.** በምወስድላቸውን ምግብ ለጓደኞቼ ፍትሃዊ ክፍፍል አደርጋለሁ።
**C.** በምወሰደውን ምግብ ከጓደኞቼ ጋር በፍቅር እበላለሁ።
**D.** በምወስድላቸው ምግብ ጓደኞቼን በመርዝ እገድላቸዋለሁ።

**52.** 55. በምንባቡ መሰረት የሌቦቹ ብዛት ስንት ነው? (1)

**A.** አራት
**B.** ሶስት
**C.** አምስት
**D.** ሁለት

**53.** 56. በምንባቡ መሰረት በመጨረሻ የሁሉም ሌቦች እጣ ፋንታ ምን ሆነ? (1)

**A.** ከከበርቴው በዘረፉት ንብረት የተሻለ ኑሮ ሆናላቸው።
**B.** ባለሀብቱ እጅ ከፈንጅ ሌቦቹን ስለያዛቸው አሳሰራቸው።
**C.** ሁሉም ሌቦች በመካከላቸው በምክንያት ሞተው ተገኙ።
**D.** ወደ ከተማ የሄደው ሌባ ብቻ ሲሞት ሌሎቹ ተርፈዋል።

**54.** 57. በምንባቡ መሰረት ሌሎቹ ሌቦች ወደ ከተማ የሄደውን ሌባ በምን ነው የገደሉት? (1)

**A.** በክላሽ
**B.** በገጀራ
**C.** በሽጉጥ
**D.** አይታወቅም

**55.** 58. በምንባቡ መሰረት ፋንታዬ ሲል ምን ለማለት ነው? (1)

**A.** የድርሻዬ
**B.** የራሴ
**C.** የግሌ
**D.** የወሌ

**56.** 59. በምንባቡ መሰረት ፈጅቷቸው ሲል ምን ለማለት ነው? (1)

**A.** ፈጽሟቸው
**B.** ገድሏቸው
**C.** ጨርሷቸው
**D.** አጠናቅቋቸው

— END OF EXAMINATION —